**Legal Aid ምን ሊረዳዎ ይችላል**

ህግን በተመረኮዙ የወንጀል ነክ ጉዳዮችን፤ የቤተሰብ ጋብቻ መለያየትን፤ የልጆች ማሳደጊያ አገዛ ማሰባሰብን፤ የአእምሮ ህመምን፤ የእርስ በርስ መበጣበጥን፤ እዳን፤ የቤት ችግርን፤ ማህበራዊ ደህንነትንና ኢሚግሬሽንን በተመለከተ ጉዳዮች ሁሉ ልንረዳዎት እንችላለን።

የኛ ነጻ የሆኑት የህግ አገልግሎቶች የሚያጠቃልሉት፡

- መረጃዎችን በስልክ መስጠት
- በቅድሚያ ቀጠሮን በመያዝ ፊት ለፊት ነጻ ምክርን ማግኘት
- ሕትመቶችን፣ ሰሚናሮችንና የሙያተኞች ወርክሾፕ

ከህግ አገልግሎት በተጨማሪ ሌላ የሚያስፈልግዎት ነገር ካለ፤ የሌጋል ኤድ እርዳታን ማመልከት ይቻላል፤ ነገር ግን እርዳታውን ለማግኘት ሁኔታዎችን መስፈርት ይገመገማሉ።

የሌጋል ኤድ ኢንፎርሜሽን እርዳታ ሰጪ አገልግሎት **LawAccess NSW** በስልክ ቁጥር **1300 888 529** በመደወል እንዴት ልንረዳዎት እንደምንችል ማወቅ ይቻላል።

ሆኖም የራስዎን ቋንቋ የሚናገር ሰው ማነጋገር ከፈለጉ፤ የትርጉምና አስተርጓሚ አገልግሎት (TIS) በስልክ ቁጥር 131 450 (ከጥዋቱ 9 ሰዓት እስከ ቀኑ 5 ሰዓት ድረስ) ባለው ጊዜ ውስጥ በመደወል አስተርጓሚው በቀጥታ ወደ LawAccess NSW በስልክ ቁጥር 1300 888 529 በማስተላለፍ እንዲያገናኝዎ መጠየቅ ይችላሉ።